አላህን በጠየቃችሁ ጊዜ ፊርደውስን ጠይቁት።

ከዑባዳህ ቢን ሷሚት (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "ጀነት ውስጥ መቶ ደረጃዎች አሉ። በየሁሉም ደረጃዎች መካከል በሰማይና በምድር
መካከል ያለውን ርቀት ያህል አለ። ፊርደውስ የላይኛው ደረጃ ነው። የጀነት ወንዞች የሚመነጩትም ከርሷ ነው። ከላዩዋ ያለውም
(ጣሪያዋ) ዐርሽ ነው። አላህን በጠየቃችሁ ጊዜ ፊርደውስን ጠይቁት።" [ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) በመጪው አለም ጀነት ውስጥ መቶ ደረጃዎች እንዳሉ፤ በየሁሉም ደረጃዎች መካከል የሚገኘው ርቀት በሰማይና በምድር መካከል ያለውን ያህል ርቀት እንደሆነ፤ ከነዚህ ጀነቶች መካከል ከፍተኛዋ ጀነት ፊርደውስ እንደሆነች፤ አራቱ የጀነት ወንዞች የሚመነጩትም ከርሷ መሆኑን፤ ከፊርደውስ በላይም ዐርሽ መሆኑንና ፊርደውስም ከሁሉም ጀነቶች በላይ ስለሆነች አላህን በጠየቃችሁ ጊዜ ፊርደውስን ጠይቁት ብለው ተናገሩ።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/65188